# አርሶ አደሩን ለመታደግ …!

እያሱ ጌታቸው

ክፍል አንድ

03/14/14

መስኖ ልማት ኢትዮጵያ ባለፉት ሁለት አሥርት ዓመታት ባደረገችው ፈርጀ ብዙ ጥረት ከድህነት ለመላቀቅ የሚያስችላትን ትክክለኛ አቅጣጫ መያዟ የበርካቶች እምነት ነው። ያላትን የመሬትና የሰው ሃብት በመጠቀም ግብርና መር የኢኮኖሚ ፖሊሲና ስትራቴጂ ነድፋ በመሥራት በተለይ ባለፉት አሥር ዓመታት ፈጣን የምጣኔ ሀብት እድገት ማስመዝገብ ችላለች። ቀደም ሲል ባገኘችው ለውጥ ላይ በመንተራስ የአምስት ዓመት እድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ነድፋ ትግበራ ከጀመረች ዛሬ ሦስት ድፍን ዓመታት አልፈዋል።

በእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅዱ እንደተመለከተው በተለይም ከ85 በመቶ በላይ የሚሆነው የአገሪቱ ህዝብ የሚተዳደርበትን የግብርናውን ዘርፍ ምርታማነት ማሻሻል ነው። ከዚህ አንጻር አገሪቱ ያላት  በመስኖ ሊለማ የሚችል መሬት በማልማት አርሶ አደሩን ከድህነት ለማላቀቅ የተያዘው እቅድ አንዱ ነበር።

እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ ከ5 ነጥብ 3 ሚሊዬን ሄክታር በላይ በመስኖ የሚለማ መሬት ባለቤት ነች። ይህንን ሀብት በአግባቡ ለመጠቀም በሚያስችል መልክ እየተንቀሳቀሰች ትገኛለች። ባለፉት ሁለት አሥርት ዓመታት የተሰራው የመስኖ ልማት ሥራ ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም።  በአሁኑ ወቅትም  በመላ አገሪቱ የመስኖ ልማት በላቀ ደረጃ ሥራ ላይ እየዋለ ይገኛል።

የግብርና ምርቱን በመጠን፣ በዓይነትና በጥራት በማሳደግ የምግብ ዋስትናን በአጭር ጊዜ በቤተሰብና በአገር ደረጃ ለማረጋገጥ ግብርናውን ከተፈጥሮ ዝናብ ጥገኝነት ማላቀቅ የግድ ይላል። ለዚህም ነው መንግሥት ከ1984 ዓ.ም ጀምሮ ለመስኖ ልማቱ ልዩ ትኩረት

በመስጠት የሚመራበትን ፖሊሲና ስትራቴጂ በመቅረፅ ዘርፉን ይበልጥ ለማሳደግ ጥረት እያደረገ ያለው።

የአምስት ዓመት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድን በመንደፍ ወደ ተግባር ከገባ ሦስተኛ ዓመቱ እየተገባደደ ነው። በነዚህም ጊዜያት ምርትን ማሳደግ ተችሏል። በ2002 የምርት ዘመን  ከ130 ሺህ ሄክታር ያልበለጠ ብቻ ነበር። ከ2003 ዓ.ም በፊት በዘርፉ የታየውን ውጤት መሠረት በማድረግ ከዘርፉ የሚገኘውን ጥቅም የበለጠ ለማስፋት መንግሥት ይህ አገሪቱ ካላት በመስኖ መልማት የሚችል መሬት በመቶኛ ሲሰላ 2 ነጥብ 4 ብቻ እንደነበር መረጃዎች ያሳያሉ።

መጠኑን በ2007 ወደ 15 በመቶ ያህል ለማሳደግ ነበር በእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅዱ ተቀምጦ የነበረው። ይህም ማለት 800 ሺህ ሄክታር የሚደርስ መሬትን በመስኖ ለማልማት ያለመ ነበር።

የመስኖ ልማቱን ለማስቀጠልም መጋቢት 1997 ዓ.ም በተነደፈው እቅድ መሠረት 80 ሺህ ሄክታር መሬት የማልማት አቅም ያላቸው የከሰምና የተንዳሆ ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ግንባታ በአፋር ክልል ተጀመረ።

ከሦስት ዓመት በኋላም 20 ሺህ ሄክታር መሬት ሊያለማ የሚችል የርብ ግድብ ግንባታ በአማራ ክልል ተጀመረ። በ2002 ዓ.ም ደግሞ በደቡብና ኦሮሚያ ክልሎች የጊዳቦ ግድብ ግንባታ እና ዝዋይ 10 ሺህ የሚጠጋ ሄክታር መሬትን ሊያለማ የሚችል የመስኖ ፕሮጀክት ግንባታ በመካሄድ ላይ ይገኛል።

በኦሮሚያና በትግራይ ክልሎችም የአርጆ ደዴሣ ግድብና መስኖ ልማት ጥናት ዲዛይንና ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት፣ የራያ አዘቦ ግፊት፣ መስኖ ልማት፣ የቆቦ ጊራና ግፊት መስኖ ልማት፣ አድአ በቾጠ ግፊት መስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ሥራዎች መከናወን ጀመሩ። ፕሮጀክቶቹ ሲጠናቀቁ ከ65 ሺህ ሄክታር መሬት በላይ ለማልማት ያስችላሉ ተብሎ ይገመታል።

በአማራ ክልል ግንባታው በ2004 የተጀመረው የቆጋ መስኖ ልማትና ተፋሰስ እንክብካቤ ፕሮጀክት ደግሞ 7 ሺህ 200 ሄክታር መሬትን የሚያለማ ነው። ፕሮጀክቱ በአሁኑ ወቅት ተጠናቆ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል።

በአማራ ክልል የመገጭ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት፣ ላይኛው ጉደር መስኖ ልማት፣ ዳቡስ መስኖ ልማትና ጥናትና ክለሳ ዝርዝር ዲዛይን ፕሮጀክትና የመገጭ የርብ አንገር ግድብ መስኖና ድሬይኔጅ የአዋጭነት ጥናትና የዝርዝር ዲዛይን ሥራዎች ባለፈው ዓመት የተጀመሩ አራት ፕሮጀክቶችም በሥራ ላይ ይገኛሉ። ፕሮጀክቶቹ ሲጠናቀቁም ከ20 ሺህ ሄክታር በላይ የሚሆን መሬትን ያለማሉ ተብሎ ይገመታል።

በአጠቃላይ በእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ዘመኑ የታቀዱት የመስኖ ልማት ጥናት፣ ዲዛይንና ግንባታ ሥራዎች ሁሉም በእቅድ ዘመኑ እንደሚጠናቀቁ ከግብርና ሚኒስቴር የተገኘ መረጃ ይጠቁማል።

የመስኖ ልማቱን በተጠናከረ መልኩ ለማስቀጠል በዘንድሮው የበጀት ዓመትም ለዘርፉ 11 የተለያዩ የግንባታና፣ ሦስት የጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክቶችን ለማከናወን መታቀዱን ከውሃ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር የተገኘ መረጃ ያሳያል።

የግብርና ሚኒስቴር በዘንድሮው ዓመት የልማት ሠራዊት በመገንባትና የዓመቱን የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ግቦችን በማሳካት የህዝቡን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በሁሉም የግብርና መስኮች የተደራጀ የልማት ሠራዊት ለመገንባት ጥረት እየተደረገ ነው።

የመስኖ ሥራውን በተደራጀ የልማት ሠራዊት አማካይነት መፈፀም፣ በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች እያንዳንዱ አርሶ አደር በቤተሰብ ደረጃ ቢያንስ አንድ የውሃ ባንክ ወይም የውሃ አማራጭ እንዲኖረው ማድረግ፣ የአነስተኛ መስኖ አውታሮችን ማስፋፋት፣ የአርሶ አደሩን ጉልበት በስፋት መጠቀም የሚሉት አቅጣጫዎችን በማስቀመጥ እየተሰራ ነው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የአርሶ አደሩን አመለካከትና የክህሎት ችግሮች የሚፈቱ ሥልጠናዎችን በመስጠት፣ በዝግጅት ምዕራፉ መከናወን የሚገባው እንደ ማዳበሪያ፣ ምርጥ ዘር፣ ፀረ ተባይ

መድሀኒት፣ የውኃ መሳቢያ ሞተሮችና የመሳሳሉ ግብዓቶችን በማቅረብ ምርትን ለማሳደግ ያላሰለሰ ጥረት እየተደረገ ነው።

በመሆኑም በያዝነው በጀት ዓመት አንድ ሚሊዮን የሚጠጋ ሄክታር መሬት በመስኖ ታርሶ በዘር ተሸፍኗል። ለዚህም 168 ሺህ 454 ኩንታል ዳፕ፣ 119 ሺ 800 ኩንታል ዩሪያ እንዲሁም 181 ሺ 563 ኩንታል ምርጥ ዘርፍ ጥቅም ላይ ውሏል።

ባለፈው ዓመት የአፈር ለምነትን ከማሻሻል አኳያም በኮትቻ አፈር የሚገኘውን ትርፍ ውኃ በማንጠፍጠፍ 200 ሺህ ሄክታር ያህል መሬት ማልማት ተችሏል። በዘንድሮው የበጀት ዓመት ደግሞ 1 ነጥብ 5 ሚሊዬን ሄክታር መሬት በኮትቻ አፈር ውስጥ የሚገኘውን ትርፍ ውኃ የማንጠፍጠፍ ሥራ ለማከናወን ታቅዷል።

በግብርናው ዘርፍ በእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅዱ ከታቀዱ መካከል የአፈርና ውኃ ጥበቃ ሥራዎች አንዱ ነው። በተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃ በመላው አገሪቱ ከፍተኛ የሆነ ንቅናቄ በመፍጠር የተለያዩ ሥራዎች ማከናወን ከተጀመረ ዓመታት ተቆጥረዋል።

በዚህም የማኅበረሰብ ተፋሰሶችን በማልማት በኩል ከ3 ነጥብ 77 ሚሊዬን ሄክታር መሬት ወደ 7 ነጥብ 78 ሚሊዬን ሄክታር ከፍ ለማድረግ ታቅዷል፤ ከእቅዱ ውስጥም 14 ሚሊዬን ሄክታር መሬት ላይ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃ ሥራ መከናወኑን ከግብርና ሚኒስቴር የተገኘ መረጃ ያሳያል።

በተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃ ሥራው ከእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ የተቀመጠውን ግብ ከወዲሁ ማሳካት የተቻለ ቢሆንም በቀጣይ የበለጠ አስፈላጊ በመሆኑ የተገኘውን ውጤት ለማስፋት እየተሰራ ነው። በቀጣይ ከ20 ሚሊየን ሄክታር መሬት በላይ ለማድረስ እየተሰራ ይገኛል።

ይህን ለማድረግም በህዝብ ንቅናቄ የሚካሄድውን ሥራ አጠናክሮ ከመቀጠል ባሻገር የፊዚካልም ይሁኑ ሥነ ሕይወታዊ ሥራዎች በተካሄዱባቸው አካባቢዎች የልቅ ግጦሽን የማስቀረት ተግባር ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባም ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ይጠቁማል።

በዚህም በ2005/2006 የግብርና ምርት ዘመን በመስኖ የሚለማውን መሬት መጠን እቅድ 2 ነጥብ 7 ሚሊዬን ሄክታር ለማድረስ ታቅዷል። እቅዱን ለማሳካት እያንዳንዱ ቤተሰብ ቢያንስ አንድ የውኃ ባንክ እንዲኖረው የሚያደርጉ አማራጮች ተለይተው ተቀምጠዋል። በዚህ መሠረት 70 በመቶ የሚሆነውን ቤተሰብ የውኃ ባንክ እንዲኖረው ለማድረግ እየተሰራ ነው።

ከግብርና ሚኒስቴር የተገኘ መረጃ እንደሚያሳየው በአገሪቱ በመስኖ መልማት የሚችል 5 ነጥብ 3 ሚሊዬን ሄክታር መሬት የግብርና ምርቱን በማሳደግ ሕዝቧን በየደረጃው ተጠቃሚ ማድረግ የሚያስችላት አቅጣጫ በመከተል ላይ ትገኛለች። ይህ በግብርናው የኢኮኖሚ ዘርፍ የሚደረገው ሁለንተናዊ ለውጥ ለአገሪቱ አጠቃላይ የምጣኔ ሀብት እድገት የጎላ ድርሻ ይኖረዋል።

ለአብነት ያህል በሀዋሳ አካባቢ የመስኖ ልማት እንዴት የአርሶ አደሮችን ህይወት እየቀየረ እንዳለ ማየት ይቻላል። አቶ ይመር ኢዳ ይባላሉ፡፡ በሀዋሳ ከተማ አስተዳደር በሀዊላ ቱላ ክፍለ ከተማ በዳቶ ኦዳሄ ቀበሌ ይኖራሉ፡፡ የቴክኒክና ሙያ ምሩቅ የሆኑት አቶ ይመር ኑሯቸውን በእርሻ ነው የሚመሩት፡፡ በመኖሪያ ቀያቸው ወደሚገኘው የእርሻ ቦታቸው ጎራ ብለን በነበረበት ወቅትም ከሥራቸው ፍሬ መካከል አንዱ የሆነውን የጥቅል ጎመን ምርታቸውን ሲቆርጡ ነበር የደረስነው፡፡

ሁለት ሄክታር በሚሸፍነው መሬታቸው ስድስት የቤተሰብ አባላት በሥራ ተሰማርተውበታል፡፡ በጥቅል ጎመን ቆረጣው ወቅትም የቤተሰቡ አባላት ተፍ…ተፍ ሲሉ ይስተዋሉ ነበር፡፡ አንዳንዶቹ በገጀራ የደረሱ ጥቅል ጎመኖችን ይቆርጣሉ፤ የተወሰኑት የተቆረጡትን ጥቅል ጎመኖች ከቆራጮቹ ውርዋሮሽ እየቀለቡ ይደረድራሉ፤ የቀሩት ደግሞ የሚደረደሩትን ጥቅል ጎመኖች ዝርግ የሽፉን ቅጠል ይልጣሉ፡፡ ይቆረጣል፣ ይወረወራል፣ ይደረደርና ሽፋኑ ይላጣል፡፡ የሥራው ፍጥነትና ቅንጅት ሥራውን ሥራ ሳይሆን ጨዋታ አስመስሎታል፡፡

አቶ ይመር በመሬታቸው የተለያዩ አትክልቶችንና ፍራፍሬዎችን ይተክላሉ፡፡ እነዚህ ምርቶች ዝናብ በማይዘንብባቸው ወቅቶች በመስኖ ሲለሙ በዝናብ ወቅት ደግሞ ድንችና ማሽላ እንዲሁም ሌሎች ሰብሎችን አልምተው ይጠቀማሉ፡፡ አቶ ይመር በሚያመርቱበት ቦታ አቅራቢያ ወራጅ ወንዝ ይፈሳል፡፡

አቶ ይመርና ሌሎች አርሶ አደሮችም በዋነኝነት የመስኖ ሥራቸውን የሚከውኑት በወንዙ በሚያገኙት ውኃ ነው፡፡ በሌሎችም የውኃ ምንጮችም መስኖ ይለማል፡፡ አርሶ አደሩ ህይወታቸውን መሠረታዊ በሆነ መልኩ ስለቀየረው የመስኖ ልማት ሲያስቡ ‹‹አስተዳደሩን አመስግናለሁ›› ይላሉ፡፡ የሀዋሳ ከተማ አስተዳደር የመስኖ ልማት ቴክኖሎጂን እንዲያውቁ አድርጎ ምርትና ምርታማነታቸውን ከፍ አድርጎላቸዋልና፡፡

መስኖ ውኃን ሰው ሰራሽ በሆነ አሠራር ለመሬት ወይም ለአፈር የምናደርስበት መንገድ ነው፡፡ የዘርፉ ባለሙያዎች እንደሚዘረዝሩት ከሆነና በተግባርም እንደተረጋገጠው መስኖ በርካታ ጠቀሜታዎች አሉት፡፡ በተለይ ደረቅ በሆኑ አካባቢዎችና የዝናብ እጥረት በሚኖርባቸው ወቅቶች የመስኖ ጠቀሜታ ከፍ ያለ ነው፡፡ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ከማገልገሉም በላይ እፅዋትን ከውሽንፍር፤ አፈርን ከመጠጠር ይከላከላል፡፡ አረም እንዳይኖር የማድረግ አቅሙም ከፍተኛ ነው፡፡ አፈርን ከመታጠብ (ከመከላት) ይጠብቃል፡፡ ቆሻሻ ውኃን ያስወግዳል፡፡ ሌላ በርከት ያሉ ጠቀሜታዎችም አሉት፡፡

ከላይ ለዘረዘርናቸው የመስኖ ጠቀሜታዎች ትክክለኛነት በሀዋሳ ከተማ አስተዳደር በመስኖ ተጠቃሚ የሆኑ አርሶ አደሮች አስረጅ ናቸው፡፡ አርሶ አደር በትረ ቱማቶ ቀደም ሲል ዝናብ በመጠበቅ ሲያመርቱና ኑሯቸውም ከእጅ ወደ አፍ እንደነበር ያስታውሳሉ፡፡

በመስኖ ያገኙትን ጠቀሜታ እንዲህ ሲሉ በንፅፅር ያስቀምጡታል፡፡ ”መስኖን አስተዳደራችን ካስገነዘበንና በተግባርም ካሰለጠነን በኋላ በመስኖው ብቻ በዓመት ሦስት ጊዜ እናመርታለን፡፡ ቀደም ሲል ያሳለፍነው ህይወት እንዴት እንደሚቆጭ” በማለት ይናገራሉ፡፡

እስከ ቅርብ ጊዜያት ድረስ የመስኖ ቴክኖሎጂ ለአርሶ አደራችን ህልም ሆኖ ቢቆይም ቴክኖሎጂው ከክርስቶስ ልደት በፊት እንደነበር ተረጋግጧል፡፡ የአርኪዎሎጂ ጥናቶች ዝናብ አጠር የሆኑ አካባቢዎች በጥንት ጊዜያት አካባቢያቸውን በመስኖ ያለሙና የእህል ምርት ሲያገኙ እንደነበር አመላክተዋል፡፡

ፈርኦን አሜንምኸት ሦስተኛ በነበረበት ከክርስቶስ ልደት በፊት በ1800 ግብጾች የዓባይ ወንዝን ተጠቅመው መስኖ ሲያለሙ እንደነበር ድርሣናት ይዘክራሉ፡፡ ከክርስቶስ ልደት በፊት ከሦስተኛው እስከ ሁለተኛው ሚሊኒየም ባለው ጊዜ ጥንታዊያን ኑቢያዎች (የአሁኖቹ ሱዳኖች) ሳኪያ ተብሎ በሚጠራ የውኃ መሳቢያ መሣሪያ ተጠቅመው በዓባይ ወንዝ መስኖን ያለሙም ነበር፡፡

በሀገራችንም በተለያዩ ጊዚያት እዚህም እዚያም ቢሞከርም ብዙኃኑ አርሶ አደር ግን ሰፋፊ የመንግሥት እርሻ በነበሩበት ወቅት መንግሥት በኋላም ባለሀብቱ ብቻ የመስኖ ተጠቃሚ ይመስለው ነበር፡፡ በሀዋሳ ከተማ አስተዳደር የግብርና ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ አስፋው ጎኔሶ "ቀደም ሲል በርካታው አርሶ አደር ዝናብ በሌለባቸው ወቅቶች መሬቱን ለባለሀብት ያከራይ ነበር፡፡ ምክንያቱም እሱ ዝናብ ካላገኘ ማምረት እንደማይችል በማሰቡ ነው " ይላሉ፡፡

ብዙኃኑን ተጠቃሚ የማድረግ አቅጣጫ የሚከተለው ልማታዊው የከተማው አስተዳደር ግን ችግሮችን በከፍተኛ ጥረት ፈትቶ በርካቶችን ተጠቃሚ ማድረግ እንደቻለ ነው አቶ አስፋው የሚያስረዱት፡፡

አርሶ አደር በትረ ቀደም ሲል የእርሻ መሬታቸውን ለባለሀብቶች ያከራዩ ነበር፡፡ በወቅቱ የሚያገኙት እፍኝ የማትሞላ ገንዘብና በአሁኑ ወቅት በራሳቸው መሬት ራሳቸው አምርተው ከሚያገኙት ጋር በፍፁም ለንፅፅር እንኳን የሚቀርብ አይደለም፡፡

"ከተራ ኑሮ ተነስተን እኔና ቤተሰቦቼ ሰው ሆነናል" የሚሉት አቶ በትረ በአንድ ዙር ብቻ እስከ ስድሳ ሺህ ብር እንደሚያገኙ ያስረዳሉ፡፡ "በዓመት ከወጪ ቀሪ ከሁለት መቶ ሺህ ብር በላይ አገኛለሁ" ሲሉም በኩራት ይናገራሉ፡፡

በእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅዱ በሰፈረው መሠረት በርካታ አርሶ አደሮች በመስኖ ልማት ተጠቃሚ እየሆኑ ይገኛሉ። በርካታ ግንባር ቀደም አርሶ አደሮችም ከመንግሥት ማበረታቻ እየተደረገላቸው ይገኛል።